የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥረኛ ዓመት ቁጥር ፶፱
አዲስ አበባ-ሐምሌ ፳፮ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

10th Year No. 59
ADDIS ABABA- 2nd August, 2004


ማውጫ


አዋጅ ቁጥር ፬፻፲፭/፲፱፻፺፮ ዓ.ም

የስኳር ኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ለማቋቋም
የወጣ አዋጅ ገጽ ፪ሺ፰፻፭


CONTENTS


Proclamation No. 415/2004

Sugar Industry Development fund Establishment
Proclamation ... Page ... 2805


## አዋጅ ቁጥር ፬፻፲፭/፲፱፻፺፮

## የስኳር ኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

በአገሪቱ የስኳር ልማት ለማካሔድ ምቹ ከባቢ ሁኔታ እና በዚህም ለገበያ ተወዳዳሪ የመሆን ዕድል እንዳለ በመታወቁ፣

በአሁኑ ጊዜ ልማቱ ከሚፈልገው ከፍተኛ መዋዕለ ነዋይ አንፃር የግል ባለሀብት ሊገባበት ያለመቻሉን በመረዳት፣

በሀገር ውስጥና በውጭ ገበያ የስኳር ፍላጎት እያደገ ሲመጣ አቅርቦቱ ግን ውስን በመሆኑ የተፈጠረውን ክፍተት ለመሙላት የተጠናከረ ሥራ መሰራት ስላለበት፣

መንግስት ይህን ልማት ለማከናወን እንዲችል በገንዘብ ምንጭነት የሚያገለግል ፈንድ ማቋቋም በማስፈለጉ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፶፭/፩/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## PROCLAMATION NO. 415/2004.

## A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE SUGAR INDUSTRY DEVELOPMENT FUND

**WHEREAS**, it is understood that there is a conducive environment to undertake the development of sugar and that there is an opportunity to undertake same competitively.

**WHEREAS**, the private sector lacks, at this stage, the capacity to participate in the said development on account of the high-level investment requirement,

**WHEREAS**, to bridge the gap that exists between the rising domestic and international demand for sugar and the shortage of supply calls for undertaking of concerted effort,

**WHEREAS**, the government, in order to undertake the aforestated development, wishes to establish a fund that will finance the intended investment,

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:


ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2:30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

## ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የስኳር ኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፬፻፲፭/፲፱፻፺፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

## ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

፩/«ባለስልጣን» ማለት በአዋጅ ቁጥር ፬፻፲፪/፲፱፻፺፬ የተቋቋመው የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ነው::

፪/ «ሚኒስቴር» ማለት የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ነው::

## ፫. ማቋቋም

የስኳር ልማት ፈንድ /ከዚህ በኋላ «ፈንድ» እየተባለ የሚጠራ/ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል::

## ፬. የፈንዱ ምንጭ

፩/ የፈንዱ የገንዘብ ምንጭ ንብረትነታቸው የመንግስት ከሆኑ የስኳር አምራች ኩባንያዎች በሀገር ውስጥ ከሚደረገው ሽያጭ ውስጥ ከብደቱ ፩፻ ኪ.ግ. ወይም አንድ ኩንታል ላይ ከብር ፪፻፶ /ሁለት መቶ ሀምሳ ብር/ በላይ የሚገኘው የሺያጭ ገቢ ይሆናል::

፪/ ንብረትነታቸው የመንግስት የሆኑት የስኳር አምራች ድርጅቶች ለፈንዱ የሚያስተላልፉት ገንዘብ ተከፋይ ከሆነ የገቢ ግብር ነፃ ይሆናል::

፫/ የድርጅቶቹ የማምረቻ ወጪ ከፍ ወይም ዝቅ ብሎ በንዑስ ቁጥር ፩ የተቀመጠውን ብር ፪፻፶ /ሁለት መቶ ሀምሳ ብር/ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሚኒስቴሩ ጥናት በማካሄድ ማስተካከያ ሊያደርግ ይችላል::

## ፭. የፈንዱ አጠቃቀም

ፈንዱ የተቋቋመበት ዓላማ የስኳር ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶችን ለማጥናት፣ አዳዲስ ኩባንያዎችን ለማቋቋምና ነባሮችን ለማስፋፋት ነው::



## 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Sugar Industry Development Fund Establishment Proclamation No. 415/2004."

## 2. Definition

Unless the context requires otherwise, in this proclamation

1/ "Authority" means the Public Enterprises Supervising Authority Established Pursuant to Proclamation No. 412/2002.

2/ "Ministry" means the Ministry of Trade and Industry.

## 3. Establishment

The Sugar Industry Development fund/ hereinafter referred to as "the Fund"/ is hereby established.

## 4. Source of the Fund

1/ Financial sources of the fund shall be sales proceeds of sugar in the domestic market by the government owned sugar-producing companies in excess of Birr 250 (Two hundred fifty) per quintal weighting 100kgs.

2/ The government owned sugar-producing companies are exempted from being subject to payment of Income Tax on the sum of money that is transferred to the Fund.

3/ The Ministry may vary the sum set at Birr 250.00 (Two hundred fifty) if circumstances dictate for such a variation on the basis of a study made by the Ministry.

## 5. Utilization of the Fund

The Fund shall be utilized for the financing of studies of sugar industry projects for establishing new sugar-producing companies and for the expansion of existing sugar-producing companies.

### ፮. የፈንዱ አስተዳደር

ፈንዱ መንግስት በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሰረት የሚተዳደረው በሚኒስቴሩ ይሆናል:: ሆኖም ሚኒስቴሩ የፈንዱን አስተዳደር ለባለስልጣኑ በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል::

### ፯. የፈንድ ሂሳብ

፩/ ሚኒስቴሩ ወይም የእሱ ተወካይ የሆነው ባለስልጣኑ የፈንዱን ሂሳብ በሚመለከት የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት በተለይ ይይዛል::

፪/ የፈንዱ ሂሳብ በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚወክለው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራል::

### ፰. ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጐች

ይህን አዋጅ የሚቃረን ማናቸውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሰራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም::

### ፱. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል::

አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፮ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

### 6. Administration of the fund

The Fund shall be administered by the Ministry in conformity with a directive given by the Government. However, the Ministry may delegate said power to the Authority.

### 7. Account of the Fund

1/ The Ministry or in the event of delegation, the Authority shall maintain separately complete and accurate books of accounts of the Fund.

2/ The accounts of the Fund shall be audited annually by the auditor General or by its designate.

### 8. Inapplicable Laws

No law, regulation, directive or practice shall have effect with respect to matters provided for in this Proclamation in so far it is found to be contradictory/inconsistent with this Proclamation.

### 9. Effective Date

This Proclamation shall enter into force on the date of its publication on the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 2nd day of August, 2004.**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL**
**DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**